
ሁለተኛ ዓመት ቁጥር 94 ነሐሴ 2012 ዓ.ም.
ዋጋ፡ 20 ብር
የሐረሪ ኦሊጋርኪ
በፍቃዱ ኃይሉ
ሽመሉ እብዲሳ
ማስተንፈሻው ሹም ሽር
ርዕስ አንቀፅ
ግብረ-ሰዶማዊነት ጠንቁ የበዛ ስድነት
"አገር በዐቢይ ትኩራ"
ነቢዩ ስብሐት
ፍትሕ
ለጠ/ሚር ዶር ዐብይ አሕመድ ተጽፎ የደረሳቸው ደብዳቤ ለፍትህ መጽሔት እንዲያመች ሁኖ የቀረበውንና ዋንውን ጽሁፍ ይመልከቱ
የቀበሮ ፌደራሊዝም...

ለ፦ **ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ አሕመድ**
ከ፦ **ነሲቡ ስብሐት** USA, VA (nhsibhat@gmail.com (703) 300 4302 USA)
ቀን፦ ነሐሴ 10 ቀን 2012 ዓ.ም. (August 17 2020)

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ አሕመድ በቅድሚያ የከበረ ሰላምታዬን አቀርባለሁ። እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ይህ ደብዳቤ ለእርሶና ለኢትዮጵያ ሀገራችንና ሕዝባችን የተጻፈ መልዕክቴ ነው። በግሌ ስሜቴንና የሀገራችንን ሁኔታ ላሳውቅዎ ፈለጉህ። "እግዚአብሔር ኢትዮጵያን አብዝቶ ይባርክ" ሲሉ በተደጋጋሚ ይደመጣሉና የእግዚአብሔርን ተአምርና ለሀገራችንና ለሕዝባችን ጥበቃ ያስተዋልኩት ትምህርት ይሆኖ ዘንድ ጠቁሜዎታለሁ። ሰው ማንነቱን ከራሱ በላይ የሚያውቀው ፈጣሪው ነውና ጊዜ ይወስዳል እንጂ አምላክ ፍርዱን ይሰጣል። ሰው ሰውን ያታልለዋል፣ ሰው ሰውን እያሳሳቀ ይገለዋል፣ ሰው ሰውን አምኖ ይጎዳል፣ ሰው በማንኛውም ጊዜ ሊያንጸባርቀው የሚችለው አውሬአዊ ባህሪ አለው። በጥቅሉ አንድ ሰው ኬሌላው ብቻ ሳይሆን ሰው እራሱ በራሱ ባህሪው ይለያያል። ትላንት ትሁትና አዛኝ የነበረው ድንገት ወደ አውሬነት ሲቀየር ይስተዋላል። ሰው ገንዘብና ሀብት ሲያገኝ የባህሪ ለውጥ ያሳያል፣ ሰው ስልጣን ሲይዝ ሌላ የማናውቀው ይሆናል፤ ሰው ገዳይ ሲሆን የሚያውቁትን ያጠቃል፤ ሌላም ሌላ። ይህ ሁሉ ተለዋዋጭ የሰው ባህሪ ግና ከፈጣሪ አይደበቅም። ሰውን በተለያዩ ተለዋዋጭ ባህሪያችን አታለነው፣ አዘናግተነው፣ አደናግረነው ተሳክቶልን ሊሆን ይችላል። ይህ ሁሉ ተግባራችን እምነት ላለን ልክ እንዳልሠራን ስለምናውቅ ሁሌም ያባንነናል፣ ይሰቀጥጠናል። ጸጽቶን ትምህርት የምንወስድ ከስንት አንዶች ነን። ቀደም ሲል የሰራነው አሳፋሪ ድርጊት ይበልጥ እንዳይታወቅብን ሌላ መከለያ ስንፈልግ "ከድጡ ወደ ማጡ" እንጓዛለን።

በሀገራችን ሰውን ለመግለጽ(Define) ለማድረግ ለእኔ ትውልድ ቀይ ሽብር በቂ ነው። ከእኛ ቀደምት አባቶቻችን በትንሹ በዐድዋና፣ ማይጨው ዘመን ሰውን ይገልጹታል። ስንት ጀግና፣ ቆራጥ እንዳለ ሁሉ፤ አብሮ እየበላ፣ እየጠጣ ከመቅጽበት ሀገሩን የከዳ፣ በሀገሩ ላይ ጦር የመዘዘ አይተዋልና ስለ ሰው ማንነት፣ ምንነት የራሳቸው ግንዛቤ ይኖራቸዋል። ከነሱ ቀደምት የነበሩት የአዲት ጉዲት ዘመንን ያዩ፣ በቀጣይነት የግራኝ አሕመድ ወረራ ጊዜ የነበሩ ቢኖሩ ሰውን እንዴት ሊገልጹት እንደሚችሉ መገመት አያዳግትም። አሁን የምናየው የሰው ባህሪ ደግሞ ትውልድ ይጽፉበታል።

የተከበሩ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐብይ አሕመድ ለዚህ መልዕክቴ ዋናው መነሻዬ በቅርቡ የአዲስ አበባን እንጦጦ መናፈሻ ፓርክ አስመልክተው የሰጡት የቴሌቪዥን መግለጫና ማብራሪያ ነው። እውን ከወቅቱ የሀገራችን ሁኔታ ጋር ሳገናዝበው ያማል፣ ያሳዝናል። ያለነው ቁስል ላይ ነው፣ ያለነው ሀዘን ላይ ነው፣ ሀገር ነጭ ድንኳን ተጥሎባታል፣ ቤተሰቦች ሀዘን ውጧቸዋል፣ ላያችን ውስጣችን ጥቁር ለብሷል። እውን ይህን ሀዘን፣ ሰቀቀን ተወጣንና ነው ስለ ፈረስ መጋለብ፣ ስለ ብስክሌት መጋለብ የሚወራልን? ለማድመጥ፣ ለማየት በሚዘገንን መልኩ "እርጉዝ በልጆቿ ፊት ታረደች"፣ "አባቴን ገድለው እጁን ቆርጠው ጨፍረዋል"፣ "ገድለውት አስከሬኑን ሉካንዳ ሥጋ መስቀያ ላይ አንጠልጥለውታል"፣ "እናት አባት ከነልጆቻቸው በሙሉ ተቃጥለው ተገለዋል"፣ "አስከሬኑን መንገድ ለመንገድ ጎተቱት"፣ ዳግሞ ለመጻፍ፣ ለማሰብ የሚዘገንን ጭንቅ፣ ቃላት የሌለው ስሜት። ዛሬ ሀገር ሀዘን ላይ ነች። በባህላችን አንድ ሰው ሲሞት እኮ ሰልስት፣ አርባ፣ ሰማንያ፣ መንፈቅ፣ ሙት ዓመት እየተባለ ይዘከራል። ምነው ዛሬ ቢሠራስ እውን ስለ መዝናኛ የምናወራበት ወቅት ነውን?

ሺህ ሁለት መቶ አሥራ ሁለት ኮረና ቫይረስ ወረርሽኝን ጨምሮ ሀገራችን ተደጋጋሚ ፍጅትና እንግልት በሕዝባችን ላይ የጣለበት ወቅት በመሆኑ ይህ ዓመት አልቆ፣ የነሐሴው ክረምት ኮቪድ 19ን ጠራርጎልን በሰላም ወደ ሁለት ሺህ አሥራ ሶስት ያሸጋግረን ልመና ይካሄዳል እንጂ እውን "የደላው ሙቅ ያኝካል እንዲሉ" አሁን በረሃብና በሰቀቀን ሕይወትን እየገፋ ላለ ሕዝባችን መስከረም 2013 ዓ.ም. ላይ የ10 ሚሊየን ብር እራት ዝግጅት እንደ ተስፋ ይደሰኮራል?

ጠ/ሚር ዐብይ አሕመድ በሻሸመኔና ሌሎች አካባቢዎች በቅርቡ በተካሄደው ዘርና ሃይማኖትን ተገን ያደረገ የጅምላ ፍጅት ከሞት የተረፉት እኮ ለብሰው ከሸሹበት አልባሳት በቀር ቤት ንብረት የሌላቸው በርካቶች ናቸው። መጠጊያ አጥተው በየቤተክርስቲያኑ በዚህ ክረምት ዝናብና ብርድ የተቆራመቱ አያሌ ወገኖቻችን ናቸው። እንደው በቦታው ተገኝተው እነሱን ማጽናናት ሲገባ ምነዋ መዝናናት፣ ፈረስ መጋለብ ቀልብዎን ሳበው? ምነው የልጆች እልቂት፣ የሕጻናት ያለ ወላጅ መቅረት፣ የሰው ልጅ በቆንጨራ መታረድ እንዲህ በአጭር ተዘነጋዎት? ሻሸመኔና በተለያዩ አካባቢዎች የደረሰው ፍጅትና ሀዘን ለአዲስ አበቤው ብቻ ሳይሆን፣ ለኦሮሞው፣ ለትግሬው፣ ለአማራው፣ ለደቡቡ፣ ለሐረሬው፣ ለጋምቤላው፣ ለክርስቲያኑ፣ ለሙስሊሙ ለሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደሆነ አልገባዎት ይሆን? በኢሕአዴግ 27 ዓመት አገዛዝ የተደረገውና የተፈጸመው እንደተጠበቀ በእርሶ የ28 ወራት አገዛዝ ሕዝብ መፈናቀል፣ መሰደድ፣ መገደል፣ ንብረት መዘረፍ፣ መቃጠል የየዕለት ተግባር ሆኖ ምነዋ ምን ይሻላል? ማለት ተሳንዎ። እያደረግሁ ያለሁት የሚሻለውን ነው ካሉ እንግዲያውስ ተሳስተዋል።

እውን እስክንድር ነጋና ጓደኞቹ፣ ይልቃል እና ስማቸው ያልተገለጸ ንጹሃን ምን አደረጉና ሊታሰሩ በቁ? አዎ! የተለመደው "ሕግ ያጣራዋል" የሚል በሕግ የተለመደ ማንገላታት ሲደግሙልን ሊያሳፍርዎት ይገባል። በ1997 ዓ.ም. ምርጫ መሸነፉን ሊቀበል ያልፈለገው መለስ ዜናዊ ወ/ሪት ቡርትካን ሚዴቅሳን፣ ዶክተር ብርሃኑ ነጋን፣ ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያምን፣ ዶር ያቆብ ኃ/ማርያምን፣ ኢንጅነር ኃይሉ ሻውልን እና ሌሎችን አስሮ ሲያሰቃይ፣ በሕግ ሽፋን ፍርድ ቤት ሲያመላልስ የነበረውን ሂደት ሲደግሙት እውን የጊዜ ተጠያቂ እንዳይሆኑ ስጋቴን ላጋራዎ ፈለግሁ።

የተከበሩ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ አሕመድ በወቅቱ በልጅነት ዕድሜ ላይ ቢሆኑም በ1981 ዓ.ም. የግንቦት 8 መፈንቅለ መንግሥት ወዲህ የደርግ ኢሠፓ አገዛዝ እንዳበቃለት ያስታውቃል። ግና ደርግ ከነበረው ወደ 300 ሺህ በላይ ሠራዊትና ዘመናዊ ትጥቅ አንጻር መቀሌም ቀደም ብላ በህወሓት ብትያዝ፣ በቀጣይነትም ወሎ፣ ጎንደር፣ ጎጃም እየዘለቁ አዲስ አበባ ወደ መከበብ ስትቃረብ "ሀገሪቷ ወደ ማያባራ ጦርነትና ዕልቂት ልትገባ ነው" የሚለው የሁሉም ስጋት ነበር። ይህ ሁሉ ስጋት ግን ከመቅጽበት የመንግሥቱ ኃይለማርያምን መፈርጠጥ ተከትሎ፣ የአየር ኃይል ጄቶች ወደ ጅቡቲ ሲፈረጥጡ፣ ጦር ሜዳ የነበሩ ታንኮች ወደ አዲስ አበባ እንደ ላንድ ኩርዘር ሲምዘገዘጉ፤ ሠራዊቱ ወታደራዊ መለያውን (Uniform) እየወረወረና ነዋሪውን የልብስ ያለህ እየተማጸነና ያነገበውን መሣሪያ እየወረወረ ሲበታተን፤ ከመቅጽበት የመንግሥት አቅም እንደ ጉም በነነ፣ ተነነ። ወያኔ ሰተት ብሎ ምኒልክ ቤተ መንግሥት ገባ፣ "ለሠፊው ሕዝብ ጥቅም ሲል ሬድዮ ጣቢያውን ተቆጣጠረው"። ሰው ያሰበው ቀርቶ እግዚአብሔር ካንዣበበው አደጋ ሀገራችንና ሕዝባችንን ጠበቀ። ***<u>ምልክት 1።</u>***

ህወሓት በኢሕአዴግ ስምና በጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ፈላጭ ቆራጭነት ሀገሪቱንና ሕዝቡን ማተራመስ ቀጠለ። እዚህ አልደግመውምና መለስ ዜናዊ እጅግ ከአዕምሮ የማይፋቁ አባባሎችና ንቀቶች ሀገርና ሕዝብ ላይ ተሳለቀ። በ1997 ዓ.ም. ምርጫ ውጤት ባለመቀበል እስከዛሬ ፍትህ ያላገኘውን የንጹሃን ደም በማፍሰስ እንደገና የአገዛዙን ዕድሜ አስቀጠለ። መለስ በሀገሪቷ ለዘለዓለም ፈላጭ ቆራጭ ገዢ አድርጎ እራሱን ኮፈሰ፣ የአፍሪካ መሪ እስከመሰኘት ተካበ፣ ማንነቱን ዘነጋ። ታምሜ አልጋ እይዛለሁ ብሎ ያላሰበው የኢሕአዴግ "ጀግና" አምላክ እግዚአብሔር በሰበብ አንደበቱን ከመቅጽበት ዘጋው፤ ለእልፈት በቃ። እውን መለስ ሞትን አስቦት ነበርን? ***<u>ምልክት 2።</u>***

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ያራከሱና ማንነቷን ያንቋሸሹት አቡነ ጳውሎስ የምድር ንጉሥ ሁነው ነበር። መንፈሳዊ ሕይወታቸውን ዘንግተው የጌታን ቤት የኃጢያት መፍለቂያ

አደረጉት። እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን በተገደለ ምህመናን "ሽጉጥ አወጡ" ተባለላቸው። የቢሮ ጸሐፊዎቻቸውና አስተናጋጆቻቸው የተዋቡ እንስት ናቸው የተባለላቸው የድፍረታቸው ድፍረት ቢያንሴን ጋብዘው ዐይናቸው ሲንከራተት የቪድዮ ካሜራ ቀለባቸው። ስንቱን አተራምሰው አልበቃ ብሏቸው "ዓሣ ጎርጓሪ ዘንዶ ያወጣል" እንዲሉ በህወሓት/መለስ ትዕዛዝ የእግዜር ማደሪያን ጥንታዊውን ዋልድባ ገዳም ቀሰቀሱ፣ ሊያፈርሱ ከጀሉ። እግዚአብሔር አሰባቸው፣ ተመለከታቸው የከንቱ ከንቱ መሆናቸውን አየ። እየሱስ "የአባቴን ቤት መነገጃ አደረጋችሁት" በማለት ጠረጴዛውን ገለባብጦ ነጋዴዎቹን የገለጸበት መቅሰፍት መታቸው። ሞታቸው እንኳ በመለስ ዜናዊ እረፍት ተሸፍኖ ተዋጠ። "አሟሟቴን አሳምርልኝ" ማለት ይሄኔ ነው። መቼም ገሃነም የገባ ነፍሱን ይማረው አይባልምና ይቻሉት ያሰኛል። ***ምልክት 3።***

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ይህ ሁሉ ምሳሌዬ ከደርግ አገዛዝ ጀምሮ በተለይ በወያኔ ዘመን አምላክ ሀገራችንን እንዴት እንደሚጠብቃት ምልክት አሳይቶናል። ለጊዜው ወየው ጉድ ብለን እንረሳዋለን እንጂ ለኢትዮጵያ ትንሳዬ እግዚአብሔር መንገዱን እየጠረገ እንደሆነ ቢታየዎት ብዬ ነው። ሌላ ልቀጥል።

ጠ/ሚር ኃይለማርያም ደሳለኝ ግራ ተጋብተው አገዛዛቸው ሀገርና ሕዝብን ወደ ትርምስ ሊከት እየተንደረደረና እየቀዘፈ ተጓዘ። "ኢትዮጵያ ወደ እርስበርስ ግጭት ልታመራ ነው" የሁላችንም ስጋት ሆነ። "ቄሮ፣ ፋኖ" ሌላም ቃላቶች አየሩን ሞሉት፤ ስጋት በር አንኳኳ። እውን በዚህ ፈታኝና አስቸጋሪ ወቅት የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር እሆናለሁ ብለው አስበው፣ ተዘጋጅተው፣ ታግለው ሳይሆን እግዚአብሔር ከመጣው ፈተና ሀገርና ሕዝብ ማዳኛ እርሶን ምክንያት አደረገ። ከመቅጽፈት ኢትዮጵያ! ኢትዮጵያ! ኢትዮጵያ! ተባለ፣ አረንጓዴ ቢጫ፣ ቀይ ሰንደቅ ዓላማዋ ከፍ አለ፣ ሕዝብ ድጋፉን ሰጥዎ፣ ዓለም እሰየው አልዎ። ***ምልክት 4።***

እውን እጅግ ከዘረፉት የሀገር ንብረት አንጻር፣ አንድ ለአምስት በሚል የስለላ መረባቸው ሕዝቡንና ወጣቱን ቀላልፈው እንደያዙት፣ የመከላከያና የደህንነት ኃይላቸውን በአንድ ዘር የበላይነት ጠርንፈው እንደያዙት እንዴት እንገላገላቸዋለን የተባሉት ወያኔ/ህወሓት ጦራቸው ዱላ ሁኖ አዲስ አበባንና ኢትዮጵያን ለቀው ሳይታሰብ ብን ብለው መቀሌ ይመሽጋሉ ያለ ማን ነበር? ኢትዮጵያን የማዳን ጥርጊያው መንገድ ግና በእግዚአብሔር ተተገበረ። ***ምልክት 5።***

ቀናት ሳምንትትን፣ ሳምንት ወራትን፣ ወራት ዓመትን እያስቆጠሩ ዛሬ 28 ወራት ሆኖቷል። በዚህ የአገዛዝ ዘመንዎ የተሠሩትን በጎ ተግባራት መዘርዘር ይቻላል ግና ጎልቶ የታየው ሀገሪቷ ያለችበት አስጊ ሁኔታ በመሆኑ እግዚአብሔርን የሚጠሩት ከውስጠ ከሆነ ይህ እጅጉን ሊያሳስብዎ ይገባል። ካላሳሰብዎም መለስና አባ ጳውሎስን ያየ የጌታ ፍርድ ይግባኝ የለውምና ያስቡበት።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐብይ አሕመድ በእርሶ የስልጣን ዘመን ገና ከጅምሩ ሰሜን አሜሪካ ዋሽንግተን ዲሲ ሐምሌ 20 ቀን 2010 ዓ.ም. እንደመጡ በአገኘሁት ዕድል ተጠቅሜ የወያኔ/ኢሕአዴግ ሕገ መንግሥት በተለይ አንቀጽ 39 እና የዘርና ቋንቋ አከላለል ለሀገሪቷ ጠንቅ መሆኑን ስገልጽልዎ የ27 ዓመት የኢሕአዴግ መርዘኛ ሕገ መንግሥትን ይዘው የትም እንደማይደርሱ ስጠቁሞት ነበር፤ አሁንም እደግመዋለሁ። በዚህ ሕገ መንግሥት ጥላ ሥርና፣ በዘርና ቋንቋ አከላለል ሀገር ማዳን ሳይሆን ማፍረስ የመጨረሻው ግብ እንደሚሆን አስረግጬ እንዳልነግርዎ ከላይ ያስቀመጥኩትን የእግዚአብሔርን አካሄድ እንዳልፈታተን ቆም ብለው ያስቡበት እላለሁ።

*እርሶ ስልጣን ከመያዞ በፊት ከሀገር ውጪ ኢትዮጵያን ለመበታተንና እስላማዊ መንግሥት ለመመሥረት ሃይማኖታዊ ቅስቀሳ ሲያደርግ የኖረው ጀዋር መሐመድ ሀገር ቤት ከተገባም በኋላ እያካሄደ ለነበረው ተግባርና ዲስኩር እድሜ ለስልጣኔ በየማኅበራዊ ገጹ የተቀመጠ መረጃ ነው። "ሁለት መንግሥት ነው ያለው" እያለ ከሞፈከር ጀምሮ በተለይ በጥቅምት ወር* 2012 *ዓ.ም.* *"ተከብቤአለሁ" በሚል ሰበብ በትንሹ ለ*86 *ሰዎች ሕይወት መጥፋት ተጠያቂ መሆን ሲገባው የሞቱትን ዘር ቆጠራ ሲገቡ፣ "ጀዋርን እወደዋለሁ" ሲሉ ምን ያህል ከሕዝብ ጋር ትዝብት እንደወደቁ ተገንዝበውታል? ሁሉም እየሆነ ለገጣፎ ተፈናቃይ፣ ቡራዮ ተገዳይ፣ አዲስ አበባ ዙሪያ በኦነግና በጀዋር አቀነባባሪነት እየተካሄደ ያለውን አዲስ አበባን የኦሮሚያ ዋና ከተማ አድርጎ ለመጠቅለል የሚደረገው ዛቻና ወከባ ብሎም ፍጅት አጀማመሩ ያስቆጣው የአዲስ አበባ ወጣት በእስክንድር ነጋ አማካይነት "ባልደራስን" ሲመሰርት "ጦርነት አውጃለሁ" በሚል ከእርሶ ከቶም በማይጠበቅ አባባል ለኦነግና ለጀዋር ጠበቅነቶን አጋለጡ። በአጠቃላይ ሕዝባችን ግራ በተጋባበት ዘመንና ሁኔታዎች ከአንድ ዘር ለመጣ ጥቃት እየተመቻቹ ሲመጡ ነፍሱን ይማረውና በሰኔ ወር* 2012 *ዓ.ም. አጫሉ ሁንዴሳ ተገደለ። ይህ ሰበብ ሁኖ "እጄን በእጄ" እንዲሉ አካሄዱ ስላሰጋዎት ጀዋር መሐመድ በራሶ አገዛዝ ለእሥር ተዳረገ። እርሶ ያደረጉት እንዳይመስሎ የኢትዮጵያ ትንሳዬ ጥርጊያ መንገድ "ፈጣሪ ኢትዮጵያን ይጠብቃት" እንዳሉት እየጠበቃት ነው።* ***<u>ምልክት 6፬</u>***

*ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐብይ አሕመድ ሆይ! ስለ ኢትዮጵያ ሀገራችንና ሕዝባችን መሪ ሆኑ እንጂ ሁሉም አሳቢ ነው። ታሪክ ሰራሁ ብለው ሊኩራሩ የሚገባዎት የህወሓት/ኢሕአዴግ ሕገ መንግሥትን አስወግደው ትውልድ ተሻጋሪ ኢትዮጵያዊ ሕገ መንግሥት ያጸደቁ እለት ነው። ታሪክ ሰራሁ የሚሉት ኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜት ዳግም እንዲያብብ ዘርና ቋንቋን ተገን ያደረገ አከላለል አብቅቶ በሌላ ፌደራላዊ አስተዳደር ለምሳሌ በአውራጃ፣ በተፈጥሮአዊ አቀማመጥ፣ ወይም ቤሌላ ሙያዊ ጥናት የተካለለ አስተዳደራዊ መዋቅር የዘረጉ ጊዜ ነው። "ሀገር በዐብይ ትኩራ" ሊያስብሎት የሚያስችለው ዘርና ቋንቋን ተገን ያደረገ የፖለቲካም ሆነ የሲቪክ ድርጅት በሕግ የተከለከለ ጊዜ ነው። ይህ ብዙ ውጣ ውረድ ቢኖረውም "የሚያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል" ነውና በያዙት ከአንዱ ዘር የበላይነት ወደ ሌላው መገላበጥ የትም አያደርስም። ኢሕአዴግ በሉት ብልጽግና "ያው በእገሌ" እንዳለችው ነው። እውነት እውነት እልዎታለሁ እግዚአብሔር ለኢትዮጵያ ትንሳዬ ፍርድ እየሰጠ ነውና እርሶ ድንገት ብቅ እንዳሉ "ወላድ በድባብ ትሂድና" ሁሉንም ዘር በአንድነት አቅፋ፣ ሁሉንም ሃይማኖት አቻችላ፣ የሁሉም ዘርና ቋንቋ የሆነች ሀገር፣ የሁሉም ዘር ክልል ኢትዮጵያ ሁና፣ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ሰንደቅ ዓላማዋ ብሔራዊ መለየዋ የሆነች ኢትዮጵያ መሪ ምንም የማይሳነው አምላክ ያመጣላታል።*

*ሌላው ልገልጽልዎ የምፈልገው የፈለገ ጊዜው ቢረዝም ፍትህ ምንጊዜም ድምጿን ልታሰማ እንደምትችል ነው። እንኳን የቅርቡ የኢሕአዴግ አገዛዝ የደርግ ዘመን ፍጅትና ዕልቂት ተጠያቂዎች በማንኛውም ጊዜና ቦታ ሊጠየቁ ይችላሉ። የቀይ ሽብር ተሳታፊዎቹን የከፍተኛ* 9*ኙን ቀልቤሳ ነገዎ፣ የከፍተኛ* 15*ቱን ከፈለኝ ዓለሙን፣ የጎጃሙን መቶ አለቃ ዓለሙን ፍርድ የሰማና ያየ ከፍትህ እንደማያመልጥ ሊገነዘብ ይገባል። ከሽብሬ ደሳለኝ እስከ አጫሉ ሁንዴሳ ያሉ በዘር ፍጅትና በፖለቲካ ልዩነታቸው ደብዛቸው የጠፋና የተጨፈጨፉ ወገኖች አይጠራጠሩ ፍትህ ያገኛሉ። በዚህ ጊዜ ደግሞ ተጠያቂዎቹ በወቅቱ ያሉት የአገዛዙ ቁንጮዎችና አጃቢ ፖለቲካ ድርጅቶች፣ ካድሬዎቻቸውና ሥልጣናቸውን ተጠቅመው የግፉና የግድያው ተባባሪ የሆኑ ሁሉ እንደሚሆኑ ሊገነዘቡ ይገባል። ብሔራዊ ዕርቅና ፍትህ የተለያዩ እንደሆኑ ሊገባን ይገባል። ብሔራዊ ዕርቅ ለሀገር ሉዓላዊነት፣ ለሕዝብ አንድነት ሲባል የተለያየ አመለካከት ባላቸው የፖለቲካ ድርጅቶች መካከል እንዲሁም ሌሎች*

የኅብረተሰብ ክፍሎችን አካቶ የሚካሄድ ሲሆን ፍትህ ግን ወንጀለኞችን፣ ገዳዮችን ለመዳኘት መሆኑን ጠንቅቀን እንለይ።

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር የእግዚአብሄርን ሌላው ተአምር የእዳሴው ግድብ ዐባይ ጉዳይ ነው። በኢትዮጵያ ሕዝብ ተባባሪነት የዐባይ ግድብ ለዚህ ይበቃ ዘንድ ያደረጉት አስተዋጽዖ ቀላል አይደለም፤ ሊመሰገኑም ይገባል። የዐባይ ሙሌትን አስመልክቶ በሁላችንም ላይ በግብጽ በኩል ሊካሄድ የሚችል የማሰናከል ስጋት አሳስቦን ነበር። ሆኖም አምላክ በቸርነቱ ዘንድሮ በሀገራችን የዘነበው ዝናብ ዐባይ ድምጹን አጥፍቶ ተሞላ ይባል ዘንድ መብቃቱና የግብጽም ፋከራ ለጊዜው ማድፈጥ እንደተጠበቀ “ዐባይ ኢትዮጵያን” እግዚአብሔር አሳካልን። መጨረሻውንም ያሳምርልን። አሜን! ***ምልክት 7።***

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር በቅርቡ የኦሮሞ “ክልላዊ መንግሥት ፕሬዘዳንት” አቶ ሽመልስ አብዲሳ ከኦሮሚያ ክልል ሊይቃን ጋር በአደረጉት ውይይት የአስተላለፉት መልዕክት እጅጉን አሳሳቢና በሀገራችን ላይ ምን እየተሴረ እንደሆነ ገላጭ ነው። እንደ አቶ ሽመልስ አባባል የብልጽግና ፓርቲ በኦሮሚያ የሚመራ፣ የኦሮሚያን ጥቅም በማስጠበቅ እነሱ ሚፈልጓትን ኢትዮጵያ መገንባት ነው። የትኛውን እንመን ዶር ዐብይ? እርሶ ሌላ ይላሉ። እንደ ሀገር መሪነትዎ የአቶ ሽመልስ አብዲሳን መግለጫ ሊያስተባብሉና እሳቸውንም ሊገስጹ በተገባ ነበር። አላደረጉትም። ይህ አባባልና በተለያዩ ጉዳዮች ላይ እየተደራረበ የሚከሰተውና የሚሰማው ተዳምሮ አመራሮን ብቻ ሳይሆን እራሶም ላይ ያለው እምነት እየተሸረሸረ መጥቷል። ሕዝባችን አዎ አቅም ባይኖረውም ሁሉንም ይገነዘባል። ሲወዶና ሲያከብሮ የነበረ ሕዝብ ዝም እያለዎት ነውና እረኛ ከመፈለግዎ በፊት ያስቡበት እላለሁ።

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ልጅም ብሆን የዓፄ ኃይለሥላሴን አገዛዝ አይቻለሁ፣ ደርግን ማቅቁበታለሁ፣ ኢሕአዴግን ተንገፍግፌበታለሁ፣ ዐብይን ተስፋ ሰጥቼዋለሁ። ግና ፈራሁ፤ ጨነቀኝ። ነገሮች ሁላ ተዋከቡብኝ። መንግሥት በአላት ሀገር የሰው ልጅ ጩኸት፣ የሕጻናት ዋይታ፣ የእናቶች ዑ ዑ ታ፣ የአባቶች እግዚዎታ፣ የወጣቶች ልመና፣ የሴቶች ልቅሶ ጎሊና ይረብሻል፣ እንቅልፍ ይነሳል። ሀገር ላይኖረን ነው? ያሰኛል። ግፌኞችን ጠልቼ ተሰድጄ በእርሶ አገዛዝ ዞሮ መግቢያዬ ብዬ እንዳልመጣሁ ዳግም ወጥቼ ልቅር? እንቅር? አዎ ኢትዮጵያ አትፈርስም! አካሄዱ ግን ሕይወት እያፈረሰ መሆን የለበትም፤ ከምንም በላይ የሰው ልጆች ሕይወት ሊያንገበግበን ይገባል። ዛሬ ሁላችንም ከመጣብን የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ፈጣሪ ይታገደን ዘንድ እንደ ሃይማኖታችን የምንጸልይበት ወቅት መሆን ሲገባው ሜንጫና ቆንጨራ ሰው አንገት ላይ ሲያርፍ ያቀስላል። በዚህ ቁስል ላይ ምንም እንዳልተፈጠረ ዳግም “ጭፍጨፋና ግድያ በፊትም የነበረ፣ አሁንም ያለ፣ ወደፊትም የሚኖር” የሚለውን መፈላሰፍ ይተዉትና ሀገር ከገባችበት አጣብቂኝ ለመውጣት የሚመከርበትን መንገድ ያዘጋጁ። ዕድልዎን ይጠቀሙበት። ምንም አማራጭ የሌለው ሕዝብ ግራ ገብቶት ተስፋ እንደቆረጠ፣ በውስጡ እንዳዘነ ሊገነዘቡ ይገባል። ግልጽ ሊሆንሎ የሚገባው ኢትዮጵያ አትፈርስም! ሲባል ለእኔ ኦሮሚያ ሀገር አትሆንም ማለት ነው። ኢትዮጵያ አትፈርስም! ሲባል ለእኔ ትግራይ ሀገር አትሆንም ማለት ነው። ይህ እንዲሆን የኢትዮጵያን ትንሳዔ ለማሳካት ***ምልክት 8*** ሳይመጣ ከእግዚአብሔር ጋር እራሶን ያነጋግሩ።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!
እግዚአብሔር ኢትዮጵያችንና ሕዝባችንን ይጠብቅልን!
ነሲቡ ስብሐት ሰሜን አሜሪካ ቨርጂኒያ
ነሐሴ 10 ቀን 2012 ዓ.ም. (August 17 2020)
(nhsibhat@gmail.com (703) 300 4302 USA)